በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ


## መምህር፡- መጋቤ ሃይማኖት ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ነሐሴ ፳፱ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ

## መግቢያ

- የፊታችን ረቡዕ መስከረም ፩ ቀን የኢትዮጵያንን የዘመን መለወጫ በዓል - አዲስ ዓመት (ርዕሰ ዐውደ ዓመት) እናከብራለን፡፡ ይህም በዓል የመስቀል በዓል እስከሚከበርበት በቅዱስ ያሬድ ውብ ዜማዎች በተመረጡ ቃላተ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ልዩ ምስጋና እስከምታቀርብበት እስከ መስከረም ፲፯ ድረስ የሚቆይ ፍጹም የደስታ ወቅት ነው፡፡
- በመስከረም ፩ እና ፪ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን ማዕከል በማድረግ ቅዱሳት መጻሕፍት ይነበባሉ ይተረጎማሉም፡፡
- ይህም የሆነው የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ሕይወቱ ከዚህ በታች እንደተጠቀሱት አዲስ ዓመትን የሚያመላክት ወይም የሚተረጉም ስለሆነ ነው፡፡

## 1. ጥምቀት፡-

- የመጀመሪያው ምልክት ቅዱስ ዮሐንስ የአዲስ ልደትና የሕይወት መጀመሪያ ምልክት የሆነበት ጥምቀት ነው፤ እርሱ ከጌታችን መምጣት አስቀድሞ ብዙዎችን በዮርዳኖስ ወንዝ ጌታችንም ከማስተማሩ በፊት ያጠመቀ እርሱ ነው፡፡ እኛም ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው በሕይወት በመለወጥ(በመታደስ) አሮጌውን ሰው አስወግደን አዲሱን ሰው ለመልበስ፤ በመንፈሳዊ ሕይወትም ለአዲስ ጅማሬ መነሳት ይገባናል፡፡በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለሚያስፈልገን ለዚህ መታደስ ምሳሌ የምናደርገው መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን ነው፤ በሃይማኖቱ ጸንቶ ጌታችንን አምላካችንን በሕይወቱ አምልኮትና አክብሮት ተገኝቷልና፡፡ የአዋጅ ነጋሪውንም በማሰብ ወርኃ ጳጕሜን የንስሐ ጥምቀት ስንጠመቅበት የምንገኝበት አንዱ ምክንያትም ይኸው ነው፡፡

# <u>መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ</u>

***<u>መግቢያ</u>***

***<u>2. ንስሐ፡-</u>***

- በዚህ የዋዜማ ወቅት ሁላችንም አዲስ ዓመትን በንስሐ ለመጀመር መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስን ምሳሌ ማድረግ ይገባናል፤ እውነተኛውን የንስሐና የኑዛዜ ሕይወት ይዘን ዘመኑን መጀመር ይገባናልና። የቅዱስ ዮሐንስ የመጀመሪያ ስብከቱ ‹‹መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ›› ***<u>ማቴ 3፡2፡፡</u>*** የሚል ነበር፡፡
- እኛም መንግሥተ ሰማያት ግልጥ እንድትሆንል አስቀድሞ ንስሐ መግባት ይጠበቅብናል፤ ንስሐ ለሠራነው ኃጢአት በእግዚአብሔር ሆነን የምናፈሳት እንባ ናትና፡፡
- ከእግዚአብሔር የሆነ የልብ ሐዘን ወደ ኑዛዜ፣ ኑዛዜውም ወደ ይቅርታ፣ ይቅርታውም ወደ መዳን፣ መዳኑም እግዚአብሔር አስቀድሞ በልባችን ወዳሠለጠናት ኋላም ወደ ምንወርሳት ወደ መንግሥተ ሰማያት ያደርሳል እንጂ ከዓለም እንደሆነው ተስፋ ወደ መቁረጥ፣ ወደ መጨነቅ፣ ራስን ወደ ማጥፋት ወዘተ አያመራም፡፡
- እግዚአብሔር በሌለበት ስለ ኃጢአታችን የምናነባበት ከእግዚአብሔር የሆነ እንባ አይኖርም፤ የእግዚአብሔር መንግሥትም አትመጣልንም፡፡ አንዱን ልባችንን ለሁለቱ ጌቶች ለእግዚብሔርና ለሰይጣን መንግሥት ልናስገዛ አንችልም፡፡
- ንስሐ ወደ እግዚአብሔር የምናድግበት ጤናማ ዕድገት እንጂ ተገቢ ባልሆነ በተሳሳተ መንገድ ከኃጢአትና ከክፋት ጋር የምንዋጋበት ጦርነት አይደለም፡፡
- ንስሐ ‹‹ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና አላቸው፡፡›› ***<u>ሉቃ 17፡21</u>*** እንደተባለ እግዚአብሔር እንዲገባበት የሰውን ልብ ለእግዚአብሔር ማዘጋጀት ነው፡፡

# መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ

- ነቢዩ ሚክያስ እግዚአብሔርን ‹‹ኃጢአታችንንም በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል።›› ሚክ 7፡19፡፡ ያለው ኃጢአታችንን ሁሉ ከፊቱ አስወግዶት በጥልቁ፣ በጥልቁ ውሃ ውስጥ እንደቀበረው ለማስረዳት ነው፡፡ በዙሪያውም ባለው ሥፍራሁሉም ድል ያደረገች ክንዱ ‹‹ማጥመድ አይቻልም›› የሚልበትን ምልክት አኑሮ ስላደረገልን በይቅርታው ኃጢአት ዳግመኛ እንዳይገዛን እንደሚያደርግልን የሚያጋግጥ ነው፡፡
- ሰይጣን ግን ወደ ጥልቁ ቆፍሮ በቀደመው ኃጢአታችን መልሶ ሊስበን ቢሞክርም ፈጽሞ አይሳካለትም፤ ዲያቢሎስ ስለቀደመውና ንስሐ ስለገባንበት ኃጢአታችን በእግዚአብሔር ፊት ክስ ቢያሰማብንም የዲያቢሎስን ክስ ከመስማትም እግዚአብሔር ጆሮውን ይመልሳል፡፡
- ዲያቢሎስ ስለቀደመው ኃጢአታችን ክስ ሲያቀርብ እገዚአብሔር ስለ ሰዎች ኃጢአት በመስቀል የፈሰሰውን ዛሬም በንስሐ የቀረቡትን የሚያነጻቸውን የልጁን ደም ያመለክተዋል፡፡ ንስሐ ስንገባ ኃጢአታችንን የጌታችን ደም ይሸፍነዋል ይደመስሰዋልና፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም።›› ሮሜ 8፡1፡፡ ያለን ለዚሁ ነው፡፡
- ንስሐ ስንገባ ስንናዘዝም የጥንቱ በእግዚአብሔር ፍቅር በጥልቁ ውስጥ ይቀበራል፡፡ የአዋጅ ነጋሪውንም በማሰብ ወርኃ ጳጕሜን የንስሐ ጥምቀት ስንጠመቅበት የምንገኝበት አንዱ ምክንያትም ይኸው ነው፡፡

## 3. መንፈሳዊ ቅንዓት፡-

- መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በእናቱ በቅድስት ኤልሳቤጥ ማኅፀን እያለ ሳይቀር ለመንፈሳዊ ቅናት ምሳሌ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡
- ቅዱስ ዮሐንስ የግመል ጠጉር ልብስ የሚለብስ፥ በወገቡም ጠፍር የሚታጠቅ አንበጣና የበረሀ ማር የሚመገብ ‹‹በምድረ በዳ የሚጮህ›› ሰው ድምፅ ነበረ፡፡

# መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ

- ሕይወቱን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ያቀረብ ፍጹም መንፈሳዊ ቅንዓት የነበረው ነቢይና ካህን ነበር፡፡ እንዲህ ያለው የመስጠት፣ ይቅር የማለት፣ የፍቅር፣ ሌሎችን የማገልገልና የመላላክ የተልእኮ ቅንዓት ቢኖረን እነዴት መታደል ይሆንልን ነበር፡፡
- ሕይወታችንን የበደልን እስራት እንፈታ ዘንድ፥ የቀንበርንስ ጠፍር እንለቅ ዘንድ፥ የተገፉትንስ አርነት እንሰድ ዘንድ፥ ቀንበሩንስ ሁሉ እንሰብር ዘንድ ብናውለው ምንኛ ባማረልን ነበር? ***ኢሳ 58፡6፡፡***
- የዛሬ ሰዎች ስለምድራዊ ሕይወታቸውና ችግሮቻቸውም በመጨነቅ ለመንፈሳዊ ነገር ጊዜ የሌላቸው ሆነዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ለመከራቸው፣ ለተበላሸ ዕድል፣ ላልተባረከ ሕይወት ተላልፈው ተሰጥተዋል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ።›› ***ሮሜ 8፡18፡፡*** ላለው ደረጃ አልበቁምና፡፡
- ይህን የሚመጣውን አዲሱን ዓመት መንፋሳዊ ቅንዓትን ግብ አድርገን በመንፈስ ቅዱስ ለመንፈሳዊ ቅንዓት ልባችን የተሞላ እንዲሆን ቆርጠን የምንነሳበት ቢሆን ምንኛ ያማረ ነው? መንፈስ ቅዱስ እንዲመራን ሽተን ከቀረብን መንፈስ ቅዱስ በውሳኔያችን፣ በድርጊታችን፣ በአገልግሎታችን፣ ከሌሎችም ጋር በምናደርገው ምክክር ሁሉ እንደሚመራን አዲሱንም ዓመት ፍሬያማ እንደሚያደርግልን እንመን፡፡

***4.ማንነትን ማወቅ፡-***

- ቅዱስ ዮሐንስ ማንነቱን በትክክል የሚያውቅ ታላቅ ምሳሌ ነው፡፡ ማንነቱን (ራሱንና) በሕይወትም ያለውን ደረጃ የሚያውቅ ነበር፡፡
- ቅዱስ ዮሐንስ ከጌታችን ቀድሞ በመንገድ ጠራጊነት ስለመጣ ብዙ ተከታዮችና ደቀ መዛሙርት ነበሩት፡፡ ‹‹ያን ጊዜ ኢየሩሳሌም ይሁዳም ሁሉ በዮርዳኖስም ዙሪያ ያለ አገር ሁሉ ወደ እርሱ ይወጡ ነበር፡፡›› ***ማቴ 3፡5፡፡***

# መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ

- በብዙ ተከታዮቹም የተነሳ ከክርስቶስ ጋር በኃይል፣ በሥልጣንና ለራሱም በሚያስፈልገው ክብር መገዳደር ቢችልም ራሱንና ማንነቱን ስለሚያውቅ ሁሉን ስለ እግዚአብሔር ክብር አደረገ እንጂ በድካም አልተገኘም፡፡
- ጌታችንም ሲመጣ አይቶ ‹‹እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ።›› ***ዮሐ 1፡29፡፡*** በማለት ተከታዮቹ እርሱን ትተው ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲከተሉ አበረታቻቸው፡፡
- ፈሪሳውያንም አንተ ክርስቶስ ነህን ብለው ሲጠይቁትም ‹‹ዮሐንስ መልሶ፦ እኔስ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ነገር ግን የጫማውን ጠፍር መፍታት ከማይገባኝ ከእኔ የሚበረታ ይመጣል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል፤ መንሹም በእጁ ነው፥ አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል፥ ስንዴውንም በጎተራው ይከታል፥ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል አላቸው። ስለዚህ ሕዝቡን በብዙ ሌላ ምክር እየመከራቸው ወንጌልን ይሰብክላቸው ነበር፡፡›› ***ሉቃ 3፡16-18፡፡***
- ስንቶቻችን እንደ ቅዱስ ዮሐንስ ራሳችንን እናውቃለን? ዛሬ ሰዎች ማናችሁ ተብለው ሲጤቁ ኢትዮጵያዊ አሜሪካዊ፣ ዐረብ፣ … ይላሉ ማን እንደሆን አናውቅም መለያ ዜግነት የለንም፡፡
- ስለእኔነት ታላቅ ምሳሌ የሚሆነን ጌታችን ነው፡፡ በምሴተ ሐሙስ ‹‹ከእናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል›› ሲል ደቀመዛሙርቱ ‹‹እኔ እሆንን›› አሉ፡፡ ያም ማለት በዓለት ላለው ውጥንቅጥ ምክንያቱ እኔ እሆንን? ነገሮች በተቃና መንገዱ እንዳይሄዱ እንቅፋት የምሆነው እኔ እሆንን? ከሶወች ጋር ያለኝን ግኑኝነት ያበላሸሁት እኔ እሆንን? እንደ ማለት ነው፡፡ ***ማቴ 26፡፡***
- ሌላው ***በዮሐ 13፡3-5*** ‹‹ኢየሱስ አብ ሁሉን በልጁ እንደ ሰጠው ከእግዚአብሔርም እንደ ወጣ ወደ እግዚአብሔርም እንዲሄድ አውቆ፥ ከእራት ተነሣ ልብሱንም አኖረ፥ ማበሻም ጨርቅ ወስዶ ታጠቀ፤ በኋላም በመታጠቢያው ውኃ ጨመረ፥ የደቀ መዛሙርቱንም እግር ሊያጥብና በታጠቀበትም ማበሻ ጨርቅ ሊያብስ ጀመረ።››የተጻፈልን ነው፡፡ ማን እንደሆን የታላቁ ንጉሥ አገልጋዮች መሆናችንን ስናውቅ ስለ ክብሩ ዝቅ ብለን የሌሎችን እግር እናጥባለን፡፡

# መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ

***5. ሰማዕትነት፡-***

- በመጨረሻ ቅዱስ ዮሐንስ ለሰማዕትነት ታላቅ ምሳሌያችን ነው፡፡ የክርስቶስ ተከታይ ከመሆኑ የተነሳ አንገቱ ለሰይፍ ተላልፎ ተሰጥቷል፡፡ በመስከረም ሁለት ቀን በቤ/ክ የሚነበብልን የሐዋርያት ሥራ ሄሮድስ የመጀመሪያይቱን ቤ/ክ እንዴት እንደፈተናት ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብንም እንዴት በሰማዕትነት እንደቀጣው የሚያስታውሰን ነው፡፡ ሌሎቹም በዐለቱ የሚነበቡ ምንባባት ስለ ክርስቶስ ሲሉ መከራ የተቀበሉትን ሁሉ ያነሳልናል፡፡ ዘመናችን ዘመነ ሰማዕታት ነው፡፡
- ቤተ ክርስቲያናችን ለዘመናት ለክርስቶስ ምስክሮቹ ሆነው ያረፉትን፣ እንደ መትምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ስለ እምነታቸው የተጨነቁትንና የተሰቃዩትን ታላላቅ ቅዱሳን ሁሉ በማሰብና በማክበርዋ - የሰማዕታት ቤት በመሆንዋ ትታወቃለች ይህም መታወቂያ ምልክቷ ነው፡፡
- ለማጠቃለል የቅዱስ ዮሐንስም የሕይወት ምሳሌነት መርምረን በሕይወታችን በተግባር ብናሳየው ምንኛ መታደል ነው!!! ሁላችን በጥምቀት የተመሰለውን በሕይወት መታደስን፣ በንስሐ መመላለስን፣ መንፈሳዊ ቅንዓትን፣ ማንነታችንን አውቀን በርሱ መጽናትን - የሰማዕታት እናትና ቤት በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ተተክለን መኖርን ያድለን፡፡ ዘመነ ማርቆስን የተባረከና የተቀደሰ ያድርግልን፡፡

ወደ ዘመነ ማርቆስ በሰላም ያሸጋግረን፡፡ አሜን!!!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org